የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት

የ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት

የስራ አመራር ሪፖርት

መጋቢት/2010

አዲስ አበባ

የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የሥራ አመራር ሪፖርት

መግቢያ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን መሰረት የመንግሥት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ መ/ቤቱ ለመ/ቤታችን የላከውን የ2009 በጀት ዓመት የሂሣብ መግለጫ ኦዲት አድርገናል።

ዓላማ

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የመንግሥት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱበት ለማድረግ ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው የዓለም አቀፍ የመንግስት ኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ስልት በመከተል ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ /የኦዲት አስተያየት/ ለመስጠት ያስችለናል።

ኦዲታችን የሚያካትተው፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና መመርመርን፣
- የሥራ አመራሩ የሒሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የአገልግሎቱ የሂሳብ አያያዝ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት መሆኑንና ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በስራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለፃቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል።

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን መመርመርን ይይዛል።

የሂሳብ መግለጫዎቹ ጉልህ ከሆኑ ግድፈቶች የጸዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል። አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል።

ይሁን እንጂ በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት የአሰራርም ሆነ የሂሣብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሣብ መግለጫውን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥሮችና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የመንግሥት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ሥራ አመራር ሲሆን የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው።

የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

የመንግሥት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. የገቢ ሂሳብ

1.1 ግኝት

መስሪያ ቤቱ የሰበሰባቸውን የተለያዩ ገቢዎች በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ በትክክል መመዝገቡን ለማረጋገጥ በናሙና ለኦዲት ከተመረጡት ውስጥ በድምሩ ብር 12,322,088.90 ከተንቀሳቃሽ እና ተንቀሳቃሽ ካልሆኑ ንብረቶች ሽያጭ የተገኘ ገቢ እንዲሁም ብር 20,920,555.30 ልዩ ልዩ ገቢዎች በአጠቃላይ ብር 33,242,644.20 የያዙ በቁጥር 203 የገቢ ትራንዛክሽኖች በIFMIS የሂሳብ አያያዝ ስርዓት ተከታታይ የገቢ ደረሰኝ ቁጥር ተሰጥቷቸው በክሬዲት የተመዘገቡ ቢሆንም የሰነድ ማስረጃ ሳይቀርብና መግለጫ ሳይሰጥ ብር 33,242,644.20 በዴቢት በመመዝገብ በገቢ የተመዘገበው ሂሳብ እንዲጠፋ የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 1 ተያይዟል)

ሥጋት

በፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት መሰረት የሂሳብ ልውውጥ የተደረገ ለመሆኑ መነሻ የሂሳብ ሰነድ ሳይኖር እና ተገቢው መግለጫ ሳይሰጥ ምዝገባ የሚደረግ ከሆነ እንዲሁም ያለምንም የሰነድ ማስረጃ እና መግለጫ ሳይሰጥ የተመዘገበውን መሰረዝ አግባብ ካለመሆኑ በተጨማሪ ምዝገባውን መሰረት በማድረግ የሚዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎችና ሪፖርቶች ተዓማኒነትም ሆነ ተቀባይነት ሊኖራቸው አይችልም ፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ማንኛውም ሂሳብ ከመመዝገቡ በፊት የሂሳብ ልውውጥ የተደረገ ለመሆኑ መነሻ የሂሳብ ሰነድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ስለሆነም አስቀድሞ በገቢ የተመዘገበው ሂሳብ እንዲጠፋ የተደረገበት ምክንያት የሚገልጹ ሰነድ ማስረጃዎች ሊቀርቡ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

ሀ. ከጨረታ ሰነድ ሽያጭ የተሰበሰበ ገቢን አስመልክቶ በአባሪ 1 ተራ ቁጥር 3፣13፣16፣19፣እስከ 29፣3 እስከ 34፣46 እስከ 49፣52 እስከ 56፣60፣69 እስከ 114፣ ከ117 እስከ 124፣27፣28፣130 እስከ 142፣144፣146፣147፣148፣150፣152፣154፣155፣159 እስከ 164፣166፣169፣እስከ178፣180፣181፣182፣188 እስከ 192፣194 እስከ 203፣ያሉት ገቢዎች በአመዘጋገብ ችግር የተፈጠረ ሲሆን ማለትም፡-

- በIFMIS ሲስተም ሲመዘገብ ሪሲት (Receipt data) እና (GL data) በመለያየቱ ምክንያት ሪቨርስ ተደርጎ የተስተካከለ መሆኑን፣
- ሁለቱ ካሸሮች ያሉን ስለነበር ገቢ ሲሰበሰብ የካሸሮቹ ሰብ-አካውንት ስለነበረ ሪቨርስ በማድረግ የተስተካከለ መሆኑን እና፡-
- የጨረታ ሰነድ ሽያጭ ሂሳብ መደብ ስህተትን ለማስተካከል ሪቨርስ ያደረግን ሲሆን ለወደፊቱ በተሰጠን አስተያየት መሰረት በጥንቃቄ በመስራት ስህተት እንዳይፈጠር ጥረት እናደርጋለን፡፡

ለ. ካገለገሉ ንብረት ሽያጭ ገቢን አስመልክቶ አባሪ 1 ተራ ቁጥር 1እስከ 4፣6 እስከ 12፣18፣31፣35 እስከ 45፣50፣51፣ 57፣ 58፣ 59፣ 61እስከ 68፣ 115፣ 116፣ 125፣ 126፣ 129፣ 143፣ 145፣ 149፣ 151፣ 153፣ 156፣ 158፣ 165፣ 179፣ 183 እስከ 187፣193፣ ያሉት ደግሞ ከላይ የተጠቀሱት ስህተቶች እንዳሉ ሆነው፡-

- አንድ ተጫራች የጨረታ ማስከበሪያ አሰርቶ በጨረታ ላይ ተወዳድሮ አሸናፊ ሲሆን ያሸነፈበት ዋጋ ለማሟላት ተጨማሪ CPO ሲመጣ ሁለቱም CPO በድምሩ ገቢ ተሰርቶለት ወደ ባንክ ሲተላለፍ ባንኩ ገቢውን በ CPO ቁጥር መዝግቦ ስለሚያሳይ ከባንኩ ጋር ሂሳብ ለማስታረቅ በIFMIS System online reconcile ስለሚደረግ በተናጠል እንደገና ለመመዝገብ መጀመሪያ በጥቅል የተያዘውን ሪቨርስ በማድረግ በተናጠል ሲመዘገብ የተፈጠረ ነው፡፡

ሐ. መስሪያ ቤቶች ግዥ እንዲፈጸምላቸው ገቢ የሚያደርጉትን በተመለከተ በአባሪ 1 ተራ ቁጥር 30 የተመዘገበውን አስመልክቶ ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ የላቦራቶሪ ዕቃዎች ግዥ እንዲፈጸምላቸው ወደ አካውንታችን ብር 2,000,000.00 ገቢ እንዲያደርጉ ተጠይቆ ገቢ የተደረገ ሲሆን ይህ ብር በIFMIS System ሲመዘገብ ገቢ የቆረጠው ባለሙያ በ2 ሚሊዮን መመዝገብ ሲገባው 20 ሚሊዮን አድርጎ በመመዝገቡ እና የሂሳብ መደቡን በ5054

መያዝ የነበረበትን በ 1451199 በመመዝገቡ ስህተቱን ለማስተካከል ሪቨርስ የተደረገ መሆኑን እንገልጻለን፡፡በአጠቃላይ በገቢ መመዝገብ ዙሪያ የተፈጠሩ ስህተቶች እንዳይፈጠሩ የተሰጠንን የማስተካከያ ሀሳብ ተቀብለን ተግባራዊ እናደርጋለን፡፡

የኦዲተሩ አስተያየት

በገቢ የተመዘገበ ሂሳብ ከመዝገብ እንዲጠፋ (Reverse) የተደረገበት ማስረጃ (print out) እንዲቀርብ ቢጠየቅም ከኢፍሚስ ሲስተም ላይ ማውጣት እንደማይቻል በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ Reverse ለተደረገ ሂሳብ ማስረጃ ከሲስተሙ ማውጣት የሚቻል በመሆኑ የተሰጠው ምላሽ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡በመሆኑም ሪቨርስ ለተደረገው የገቢ ሂሳብ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ ሂሳቡ እንደተባለው ከገቢ የተሰረዘ መሆኑን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

2. የወጪ ሂሳብ

2.1 በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ ወጪ

ግኝት

የወጪ ሂሳቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት ለ2009 በጀት ዓመት በተፈቀደው የበጀት ድልድል መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ለትራንስፖርት አገልግሎት ተከፍሎ ማስረጃ የቀረበለት ብር 20,315.00 በሂሳብ መደብ 2221102 መመዝገብ ሲገባው በተከፋይ ሂሳብ መደብ 6171101 ካለሂሳብ መደቡ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

በተጨማሪም ከላይ የተመለከተው ብር 20,315.00 ወጪ ተደርጎ የተከፈለው በአደራ ከተቀመጠ ሂሳብ ላይ መሆኑ ታውቋል፡፡

ሥጋት

ማንኛውም ሂሳብ የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት አለመመዝገብ በሂሳብ አያያዝና በበጀት አስተዳደር ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ወጪዎች ከመመዝገባቸው በፊት ለወጪው በጀት መያዙንና በትክክለኛ የሂሳብ መደብ ለመመዝገቡ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

ለትራንስፖርት አገልግሎት ተከፍሎ ማስረጃ የቀረበለትን ብር 20,315.00 በሂሳብ መደብ 2221102 መመዝገብ ሲገባው በተከፋይ ሂሳብ መደብ 6111101 የተመዘገበ ለተባለው ማስተካከያ የሚሰራለት ይሆናል በማለት ገልጸዋል፡፡

2.2 <u>የሰዓት መቆጣጠሪያ ሳይቀርብ ለመስተንግዶ የተፈጸመ ክፍያ</u>

<u>ግኝት</u>

ለመስተንግዶ አገልግሎት የወጣው ሂሳብ በፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 14 ን.አንቀጽ 4 እና 7 መሰረት ተገቢው የተሟላ ደጋፊ የክፍያ ሰነድ የቀረበለት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በኢትዮጵያ ስራ አመራር ኢንስቲትዩት በተለያዩ ቀናት ስልጠና ለወሰዱ ሰራተኞች በድምሩ ብር 149,663.20 ለኢንስቲትዩቱ ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም ሰልጣኞች በትክክል በስልጠናው ላይ ስለ መሳተፋቸው የሚያረጋግጥ የሰልጣኞች ስም ዝርዝር እና በሰልጣኞች ፊርማ የተረጋገጠ የሰዓት መቆጣጠሪያ ሰነድ ያልቀረበ በመሆኑ የወጪውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 2 ተያይዟል)

<u>ስጋት</u>

ሰልጣኞች በስልጠናው ላይ ለመገኘታቸው ክትትል አለማድረግ ለገንዘብ ብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በስልጠናው ላይ የተካፈሉ ሰራተኞች ዝርዝር የሰዓት መቆጣጠሪያ (Attendance) ሙሉ በሙሉ ከሰነዱ ጋር ሊያያዝ ይገባል፡፡ ማስረጃ ያልቀረበለት ክፍያም ማስረጃ እንዲቀርብለት ሊደረግ ይገባል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

እስከ አሁን ድረስ ክፍያ የሚፈጸመው አገልግሎቱ ስልጠናውን ከሚሰጥልን መስሪያ ቤት ጋር የተዋዋለውን ውል መነሻ በማድረግ ስልጠናው ከተጠናቀቀ በኋላ በሚላከው የክፍያ ጥያቄ መሰረት ነው፡፡ አቴንዳንስ በስልጠና ወቅት የተፈረመው ስልጠናውን የሰጠልን አካል ጋ ስለሚቀር እስከዛሬ ድረስ አልተጠየቀም፡፡ አቴንዳንሱን ማየት አስፈላጊ ከሆነ ስልጠናውን የሰጠልን ተቋም ጋ ማየት የሚቻል ሲሆን ለወደፊቱ በተሰጠን አስተያየት መሰረት አቴንዳንሱን ከክፍያ ሰነድ ጋር እንዲያያዝ እናደርጋለን፡፡

2.3 <u>የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ</u>

<u>ግኝት</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች ለመስሪያ ቤቱ አገልግሎት የዋሉና ተገቢው ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

በናሙና ለኦዲት ከተመረጡት የወጪ ሂሳቦች ውስጥ ለአየር ትኬት ግዥ ብር 214,366.00 ፣ ለማስታወቂያ ብር 4,579.00 እንዲሁም ለተለያዩ ወጪዎች ብር 50,000.00 በድምሩ ብር 268,945.00 የያዙ የወጪ ሰነዶችና ደጋፊ የክፍያ ማስረጃዎች ለኦዲት ሊቀርቡ አልቻሉም፡፡

<u>ስጋት</u>

ለኦዲት ስራ የተጠየቁት የሂሳብ ሰነዶችና ደጋፊ የክፍያ ማስረጃዎች ሊቀርቡ ባለመቻላቸው ክፍያው መ/ቤቱ ለተጠቀመበት አገልግሎት የዋለ መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ለኦዲት እንዲቀርቡ የሚጠየቁ ማስረጃዎች በተፈለጉ ጊዜ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ለኦዲት ስራ ተጠይቀው ያልቀረቡት የሂሳብ ሰነዶች በአፋጣኝ እንዲቀርቡ መደረግ አለበት፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

ደጋፊ የክፍያ ሰነዶች ያሉን ስለሆነ የወጪ ሰነዶቹን ኮፒ ከዚህ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

<u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

የወጪ ማስረጃዎች ተያይዘዋል የሚል ምላሽ የተሰጠ ቢሆንም ተያይዘው ያልቀረቡ በመሆኑ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

3 ተሰብሳቢ ሂሳብ

ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ

3.1 ግኝት

በፌዴራል መንግስት ሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 4 (ለ) መሰረት ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ለመከታተል ተገቢው የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት እንዳለበት እና የስራ ማስኬጃ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ ሊወራረድ እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ በሰኔ 30/2009 በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ከተመለከተው ብር 494,627,863.47 ውስጥ ብር 433,332,049.31 ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ድረስ የተወራረደ ሲሆን ቀሪው ብር 58,763,114.41 በወቅቱ ያልተወራረደ መሆኑ ታውቋል፡፡ ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ሂሳብ መደብ	መግለጫ	ተሰብሳቢ ሂሳብ የቆየበት ጊዜ			ጠቅላላ	ኦዲቱ እስኪጠናቀቅ የተወራረደ ሂሳብ	ጠቅላላ ያልተወርረደ ቀሪ ተሰብሳቢ ድምር
			ከ 1-1 ዓመት ወር በታች	ከ1 ዓመት - 5 ዓመት	ከ5 ዓመት እስከ 10 ዓመት			
1	5217201	ሌተር ኦፍ ክሬዲት		176,925,898.37	275,816,610.93	452,742,509.30	397,592,023.53	55,150,485.77
2	5217205	ለአቅራቢዎች የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ		15,817.61		15,817.61	434.03	15,383.58
3	5217301	ለሰራተኞች የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ	1000.00	688.59	300.00	1,988.59	1,988.59	-
4	5217399	ሌሎች ተሰብሳቢ ሂሳቦች		41,867,547.97	-	41,867,547.97	38,270,302.91	3,597,245.06
		ድምር	**1000.00**	**218,809,952.54**	**275,816,910.93**	**494,627,863.47**	435,864,749.06	58,763,114.41

ሥጋት

በተሰብሳቢ ሂሳቦች ላይ ተገቢው ቁጥጥር እና ክትትል ካልተደረገ የመንግሥት ገንዘብ ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ ካለማስቻሉም በላይ ገንዘቡ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች እንዲሰበሰቡ፤ ሊሰበሰቡ የማይችሉ ከሆነ ግን በመመሪያው መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች በወቅቱ እንዲወራረዱ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

- በአቅራቢዎች የተሰጠ ቅድመ ክፍያ በሂሳብ መደብ 5117205 ያልተወራረደ 15,383.58 ሲሆን ይህን እንዲወራረድ በተደጋጋሚ ዱባይ ለሚገኘው ለኢትዮጵያ ጄነራል ቆንጽላ ጽ/ቤት እና ለውጭ ጉዳይ ሚ/ር ደብዳቤ የተጻፈ ሲሆን ገንዘቡን ተመላሽ ለማስደረግ ተገቢውን ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡ በተለያየ ጊዜ እንደገለጽነው ቀሪው ሂሳብ በአስቸኳይ እንዲወራረድ ለኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክ አገልግሎት በተለያየ ጊዜያት የተጠየቀና ክትትል እየተደረገ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

3.2 ሂሳቡ ስለመወራረዱ ወይም ገንዘቡ ተመላሽ ለመደረጉ ማስረጃ ያልቀረበለት የኤልሲ ሂሳብ

ግኝት

ለተለያዩ አለም አቀፍ ግዢዎች የሚከፈቱ ኤልሲዎች ግዢው ከተጠናቀቀ በኋላ በአግባቡ የሚዘጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በቀን 29/09/06 በኤልሲ ቁጥር 1415764540 ብር 89,573,548.12 ለ144 መኪኖች ግዢ የተከፈተ ሲሆን ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ብር 89,421,693.95 ማስረጃ የቀረበ ሲሆን ቀሪው ብር 151,854.17 ስለመወራረዱ ወይም ገንዘቡን ላስያዘው አካል ተመላሽ ስለመደረጉ ማስረጃ ሊቀርብለት አልቻለም፡፡

ሥጋት

ኤልሲ የተከፈተላቸው ሂሳቦች በወቅቱ እንዲዘጉ ካልተደረገ ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ቀሪው ሂሳብ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተጣርቶ እንዲዘጋ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

ብር 151,854.17 በወቅቱ በገ/ኢ/ት/ ሚኒስቴር ብሎክድ የሆነ መሆኑን እንገልጻለን በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

የኦዲተሩ አስተያየት

በገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር ብሎክ ለመደረጉ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

3.3 ለተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሳቦች ተቀጽላ ሌጀር ያልተከፈተላቸው ስለመሆኑ

ግኝት

ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ መ/ቤቶች ለግዥ ተብሎ በአገልግሎቱ አካውንት ገቢ ለሚደረገው እና ለሚከፈለው ሂሳብ በየመ/ቤቶቹ ስም የተከፈተ ተቀጽላ ሌጀር ባለመኖሩ የሂሳቡን እንቅስቃሴ ለማወቅ አልተቻለም፡፡

ስጋት

በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የሚደረገውን ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ተቀጽላ ሌጀር በየመ/ቤቶቹ ስም ተከፍቶ ያሰገቡትን ገቢ እና የተፈጸመውን ክፍያ እንዲሁም ከወጪ ቀሪው በዝርዝር እንዲታይ መደረግ ይኖርበታል፡፡

4 ተከፋይ ሂሳብ

4.1 ግኝት

በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 5 በተመለከተው መሰረት ተከፋይ ሂሳቦችን ለመከታተል ተገቢው የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋቱንና መሥሪያ ቤቱ ተከፋይ ሂሣቦችን በገባው ግዴታ መሰረት በወቅቱ የሚከፍል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፤

በሰኔ 30/2009 በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ከተመለከተው ውስጥ በድምሩ 53,982,806.33 ለሚመለከተው አካል ያልተከፈለ መሆኑ ታውቋል፡፡ከአደራ ሂሳብ ብር 415,962,545.03 ለመወራረዱ ማስረጃ የቀረበ ቢሆንም በጥቅል የተወራረደ በመሆኑ ከማን ሂሳብ ላይ እንደተቀነሰ ለማወቅ አልተቻለም፡፡ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ለባለጥቅሙ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ መግለጫ

ተ.ቁ	ሂሳብ መደብ	መግለጫ	የተከፋይ ሂሳብ የቆየበት ጊዜ		ጠቅላላ	ኦዲቱ እስኪጠናቀቅ የተወራረደ ሂሳብ	ጠቅላላ ያልተከፈለ ቀሪ ሂሳብ ድምር
			ከ 1ወር -1 ዓመት ወር በታች	ከ1 ዓመት - 5 ዓመት			
1	6171101	(ልዩ ልዩ ተከፋዮች)	359,310.16		359,310.16	-	359,310.16
2	6174208	የተጨማሪ እሴት ታክስ	3,219.57		3,219.57	3,219.57	-
3	6174299	የአደራ ሂሳብ	224,117,877.62	245,468,163.58	469,586,041.20	415,962,545.03	53,623,496.17
4	6172105	ዊዝሆልዲንግ ታክስ	226.96		226.96	226.96	-
ድምር			224,480,634.31	245,468,163.58	469,948,797.89	415,965,991.56	53,982,806.33

ስጋት

ተከፋይ ሂሣብ በወቅቱ ካልተከፈለ ጊዜው በረዘመ ቁጥር የዕዳ ክምችት የሚፈጠር በመሆኑ ዕዳውን ለመክፈል ሊያዳግት ስለሚችል በገንዘብ አስተዳደር ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

መከፈል የሚችሉት ተከፋዮች በወቅቱ እንዲከፈሉ፤ መከፈል የማይችሉት ደግሞ በመመሪያው መሰረት እንዲሰረዙ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

በሂሳብ መደብ 6171101 ልዩ ልዩ ተከፋይ የሚባለው የIFMIS ሲስተም ባይ ዲፎልት አካውንት የሚጠቀምበት ለማንኛውም ኢንቮይስ ስናዘጋጅ እና ክፍያ ሲፈጽም ራሱን በራሱ እየመዘገበ የሚሄድ ነው እንጂ እንደደሌሎቹ የሂሳብ መደብ የምንጠቀምበት አይደለም ፡፡ ሂሳብ መደቡ ራሱን በራሱ ክፍያዎች ሲፈጸሙ የሚጠፋ ይሆናል፡፡

5. **<u>በጀት</u>**

<u>ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት</u>

<u>ግኝት</u>

ለመ/ቤቱ በ2009 በጀት ዓመት ለየፕሮግራሞቹ የተመደበው የመደበኛ በጀት ሂሳብ በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ሥራ ላይ ከዋለው ሂሳብ ጋር ሲነጻጸር በየፕሮግራሙ በተመለከቱት አንዳንድ የወጪ አርዕስቶች ከ10% በላይ

- በፕሮግራም 01/01 ብር 846,949.09፤
- በፕሮግራም 02/01 ብር 895,504.67፤
- በፕሮግራም 02/01 ብር 134,433.35

በድምሩ ብር 1,876,887.11 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ ታውቋል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 4 ተያይዟል)

<u>ሥጋት</u>

የተፈቀደው በጀት በአግባቡ ካልዋለ የመ/ቤቱን የሥራ ክንውን ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት አያመለክትም።

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

- በፕሮግራም/ ሂሳብ መደብ 2111104 የተፈቀደው በጀት ለሚወገዱ ንብረቶች መጓጓዣ የሚሆን ኮንትራት ሰራተኛ ሲሆን በበጀት ዓመቱ የኮንትራት ሰራተኛ ባለመኖሩ ነው፡፡
- በሂሳብ መደብ 2241107 ሙሉ በሙሉ ክፍያው በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የተከፈለ ስለሆነ በጀቱ ስራ ላይ ሳይውል ቀርቷል፡፡
- በፕሮግራም 2 በሂሳብ መደብ 2241101 የተያዘው በጀት ለግምገማ የተያዘው በበጀት ዓመቱ ግምገማ የሚያካሂዱ ድርጅቶች ባመኖራቸው ገንዘቡ ጥቅም ላይ ሳይውል ቀርቷል፡፡ በዚሁ ፕሮግራም በሂሳብ መደብ 2241102 ለመኪና ኪራይ የተያዘው በጀት ሲሆን መኪናው ከሌላ ስለተገኘ በጀት ጥቅም ላይ አልዋለም፡፡
- በፕሮግራም 3 በሂሳብ መደብ 2241105 ለዕቃ መጓጓዣ የተያዘ በጀት ሲሆን በበጀት አመቱ የሚጓጓዝ ንብረት ባለመኖሩ ጥቅም ላይ ያልዋለ በጀት ሌሎች የሂሳብ መደብ በ3ቱም ፕሮግራም የተያዙት ከሞላ ጎደል በተለያዩ ምክንያቶች ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ የዋለ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

6. <u>ልዩ ልዩ</u>

6.1.<u>በትክክለኛው የቼክ ቁጥራቸው በመዝገብ (TR) ላይ ያልተመዘገበ ግኝት</u>

መሥሪያ ቤቱ የባንክ ሂሳብ (አካውንት) በቼክ ወጪ ለተደረጉ ሂሳቦች ተገቢው ምዝገባ የሚከናወን መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ለኦዲት ከተመረጡት ውስጥ .በድምሩ ብር 518,714,303.78 ዋጋ ያላቸው የተለያዩ ክፍያዎች የቼክ ቁጥራቸው በገንዘብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ በትክክል ያልተመዘገበ በመሆኑ ለክትትልና ለቁጥጥር አዳጋች መሆኑ ታውቋል፡፡(ለዝርዝሩ አባሪ 5 ተያይዟል)

ሲስተሙ አዲስ በመሆኑ በ system የተሰሩ ክፍያዎች በሆነ ምክንያት ስህተት ሆነው ሲገኙ ከ System cancel ሲደረጉ የተሰጠው ቼክ ቁጥርም cancel ሆኖ የሚቀጥለውን ቼክ ቁጥር ይጠቀማል፡፡ በወረቀት የተሰራው ቼክ ግን Void ስለማይሆን ከሲስተሙ ጋር መጣጣም ባለመቻሉ የተፈጠረ ነው፡፡

<u>ሥጋት</u>

የሌጀር ምዝገባን ከባንክ ሂሳብ ምዝገባ ጋር ማመሳከር ባለማስቻሉ የቼክ ሂሳቦችን ለመቆጣጠር እና ለመከታተል አዳጋች ይሆናል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በቼክ ወጪ የተደረጉ ሂሳቦች በትክክለኛው የቼክ ቁጥሩ በመዝገብ (TR) ላይ ሊመዘገብ የሚገባ ሲሆን የፋይናንስ ክፍሉ ለወደፊቱ ተመሳሳይ የአሰራር ግድፈት እንዳይደርስ ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

ሲስተሙ አዲስ በመሆኑም በ system የተሰሩ ክፍያዎች በሆነ ምክንያት ስህተት ሆነው ሲገኙ ከ system cancel ሲደረግ የተሰጠው ቼክ ቁጥርም cancel ሆኖ የሚቀጥለው ቼክ ቁጥር ይጠቀማል፡፡በወረቀት የተሰራውን ቼክ ግን void ስለማይሆን ከሲስተሙ ጋር ማጣጣም ባለመቻሉ የተፈጠረ ነው ፡፡ ለወደፊቱ በተሰጠን አስተያየት መሰረት ግድፈት እንዳይፈጠር ጥንቃቄ እናደርጋለን፡፡

6.2 <u>በተሰረዙ የቼክ ቁጥር ተመዝግቦ የተገኘ የባንክ ሂሳብ</u>

<u>ግኝት</u>

የባንክ ሂሳብ ምዝገባ በአግባቡ የሚከናወን መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ከተመረጡት የቼክ ሂሳቦች ውስጥ በድምሩ ብር 2,409,724.12 በልዩ ልዩ ምክንያት ተመላሽ የተደረጉ ወይም በተሰረዙ (ቮይድ) ቼኮች ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡(ለዝርዝሩ አባሪ 6 ተያይዟል)

<u>ሥጋት</u>

የባንክ ሂሳብ ክፍያዎች በትክክለኛው የቼክ ቁጥራቸው እንዲመዘገቡ ካልተደረገ የባንክ ሂሳብን ለመከታተልም ሆነ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ ለማዘጋጀት አዳጋች ሊሆን ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በባንክ ሂሳብ ወጪ ለሚደረጉ ክፍያዎች ቼክ ተዘጋጅቶ በሚመለከተው ክፍል ተፈርሞ ወጪ ሲሆን ትክክለኛው ቼክ ቁጥሩ በመዝገብ(TR) ላይ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

የወረቀት ቼክ ቮይድ ሲደረግ በሲስተም ላይ የተሰጠውን ቼክ ቁጥር ባለመቀየሩ ምክንያት የተፈጠረ ሲሆን በገንዘብ ለውጥ በኩል የተፈጠረ ችግር

የለም፡፡ ለወደፊቱ በተሰጠን አስተያየት መሰረት ጥንቃቄ በማድረግ እንዲመዘገብ ጥረት እናደርጋለን፡፡

6.3 <u>በኦዲት ግኝቶች ላይ ስለተወሰደ የእርምት እርምጃ</u>

<u>ግኝት</u>

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ክፍል አምስት አንቀጽ 17/3 መሰረት ኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች፣ የማሻሻያ ሃሣቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸው እርምጃ ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለጽ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ እንዳለባቸው የተደነገገ ሲሆን በተጨማሪም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 የመንግስት መ/ቤት ኃላፊ በውጭ ኦዲተሮችና እንዲሁም በውስጥ ኦዲት አገልግሎት በሚቀርቡት የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ላይ እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡በመሆኑም የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የሚኒስቴር መ/ቤቱን የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት በማድረግ በሰጠው የኦዲት ውጤትና የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት ተገቢው እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከታች የተመለከተው እርምጃ ሳይወሰድበት ተገኝቷል፡፡

<u>ግኝት</u>

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 8 (ሀ)- የሂሳብ ሪፖርት ከመዘጋጀቱ በፊት የአጠቃላይና የተቀጽላ ሌጀር ሚዛን ትክክለኛነቱ መረጋገጥ አለበት፣ (ለ)- ትክክለኛነቱ የተረጋገጠው ሌጀር ሚዛን ሂሳብ ወደ ገቢ፣ ወጪ፣ ዝውውር ተከፋይና ተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ ላይ በትክክል መተላለፍ እንዳለባቸው ይገልፃል ፡፡ ይሁን እንጂ በበጀት ዓመት የታዩት የተከፋይ ሂሳብ ከወጪ ቀሪዎች ወደ ቀጣዩ በጀት ዓመት በትክክል መተላለፋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በሂሳብ መደብ በ6174299 (የአደራ ሂሳብ) የተመለከተው ከወጪ ቀሪ እና በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት በተደረገው መካከል

የሚታይ ልዩነት ብር 25,374,426.75 ተጣርቶ የሂሳብ ማስተካከያ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ አለመወሰዱ ታውቋል፡፡

<u>ስጋት</u>

በኦዲት ሪፖርቱ ላይ እርምጃ ባለመወሰዱ ምክንያት የውስጥ ቁጥጥሩና የአሰራር ስርዓቱ ላይ አሜኔታ እንዳይኖረውና ለተጨማሪ ብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በመ/ቤቱ የሚታዩት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እንዲቀረፍ ብሎም ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን የሥራ አመራሩ በኦዲት በሚሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት የእርምት እርምጃ በመውሰድ የበኩሉን አስተዋፅኦ ሊያበረክት ይገባል፡፡

በኦዲቱ ወቅት ለተደረገልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን